# ስለ ጣና ሐይቅ መበከልና የመድረቅ አደጋ

የጣና ሐይቅ በኢትዩጵያ ትልቁ የሐሩር አውራጃ ንፁሕ ውሃ ሐይቅ፣ ማለትም ጨዋማነት የሌለው፤ የታላቁ አባይ ወንዝ መጋቢ፣ በውስጡ 37 ደሴቶችን ይዞ የብርቅዬ ዕፅዋትና እንስሳት ምችጌ መኖሪያ፣ የኢትዩጵያ ጥንታዊት የኦርቶዶክስ ክርስትና ገዳማት ያሉበት፤ ሰፊ የታሪክና ባሕል ቅርሶች ግምጃ ቤት ነው።

በጣና ሐይቅ ውስጥ 65 የዓሣ ብቸኛ ዘርያዎች እንዲሁም ከሁለት መቶ በላይ አእዋፋት ዓይነት አሉት። የጣና ሐይቅ መጋቢ ዋና ወንዞች አራት ናቸው። እነዚህም ግልገል አባይ ከሰከላ የሚነሳው፣ ረብ፣ ጉመራና መገጭ ናቸው። በተጨማሪም በሐይቁ ስፋት ላይ በክረምትና በበልግ ወራት በሚዘንመው ዝናም መጠን ይሞላል። የጣና ሐይቅ ጥልቀት በአለፉት 400 ዓመታት ውስጥ እየቀነሰ መምጣቱና ለአየር ንብረት መለዋወጥ ማለትም ለዝናቡ መጠን ከፍዝቅ ማለት የተጋለጠ መሆኑ ይታወቃል።

የጣና በለስ ኃይል ማምንጭያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የጣና ሐይቅ ርዝመቱ 85 ኪሎሜትር፣ ውርዱ 70 ኪሎሜትር ሲሆን አማካይ ጥልቀቱም 9 ሜትር ያህል ሲሆን ጠቅላላ ይዘቱም 28 ቢሊዎን ኩባዊ ሜትር፣ ስፋቱም 3672 ካሬ ኪሎሜትር ነበር። የሐይቁ የውሃ ከፍታ መጠን ሊጢስ እሳት ሁለተኛ ኃይል ማመምንጭያ በመፋሰሻው ላይ በ1989 ዓ.ም በተገነባው ማገጃ (የጭያራ ጭያራ ግድብ Chara Chara weir) አማካይነት ይስተካከል ነበር።

ከሐይቁ 35 ኪሎሜትር ርቀት በስተደቡብ ምሥራቅ አቅጣጭያ ላይ የተፈጥሮ ውብ አስደናቂው እስከ 45 ሜትር ያህል ከፍታ ያህል የጢስ እሳት ፏፏቴ ይገኝ የነበረበትን አልፎ በጥልቁ ሸለቆው ውስጥ እየፈሰሰ ምሥራቃዊ አቅጣጭያውን ወደ ምዕራብ በኩል በመቀየር ወደ ሱዳንና ግብፅ ሲነጉድ ቆይቷል። ጊቦንስ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ ኢትዩጵያውያ ሌላውን ዓለምን ለሺህ ዓመታት ርስተው በሃይማኖታቸውና ነፃነታቸው ጥላቶች ተከበው ኖረዋል እንዳለው የጣና ሐይቅ እስከ ጥቂት ዓመታት ድረስ እንደ ሌሎቹ የአፍሪቃና ሌሎች አህጉራት ሐይቆች ለምሳሌ የምሥራቅ አፍሪቃው ቪክቶሪያ ሐይቅ (ዩከረዊ)፣ የቻድ ሐይቅ ወዘተረፈ በሰው ሠራሽ ብክለትና የአካባቢ ጠንቆች ያልተበከለ፣ የሥነ ምኅዳር ሚዛኑ ፈጽሞ ያልተቃወሰ ነበር።

ነገር ግን ወያኔ ትግሬ ሕወሃት ሥልጣን ከያዘ ከግንቦት ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ ባማራው ማኅበረሰብ ላይ በመላው ኢትዩጵያ ውስጥ የዘር ማጥፋትና ማጽዳት ዘመቻ እያደረገ መሆኑ፤ ያማራውን ለም አውራጃዎች እነ ወልቃይ ጠገዴ ጠለምትን ወዘተረፈ ወደ ትግሬ ክልል ያለ ሕዝቡ ፍላጎትና ስምምነት ማጠቃለሉና እንዲሁም ለተባባሪዎቹ የኦረሞ፣ የአፋር፣ የሱማሌ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ የጎሣ ክልሎች ሰፋፊና ለም ያማራ ምድርን አስረክቧቸዋል። ጥቂት በተረፈው ያማራ ክልል ተብዬውም ቢሆን እንኳ በቀጥታ የሚተዳደረው ባማርኛ ተናጋሪ ታማኝ ትግሬዎችና የሕወሓት አባላት ነው። በዘመነ ወያኔ ትግሬ ዐማራውን ሕዝብ ከፖለቲካው፣ ከኢኮኖሚውና ከማኅበረሳባዊ መድረክ ፈጽሞ ተገላይ ሲደረግ በአንጻሩ ያማራውን ሕዝብ የተፈጥሮ ሃብትና ጉልበት ለመበዝበዝ ወያነ ትግሬና ዓለም አቀፍ ተባባሪዎችና ጠባቂዎቹ ከፍተኛ መረባረብ፣ አድርገዋል፤ ያደርጋሉ።

# ማነው እምቦጭን ያመጣው?

ያማራውን ማኅበረሰብ ለመጉዳት በሰፊው ታስቦና ታቅዶ የጣና ሐይቅን ሆን ብለው በመጥፎ ወራሪ አረም እምቦጭ ወያኔዎችና የበላይ ጠባቂዎቻቸው ማስበከላቸው ፈጽሞ አያጠራጥርም።

መታወቅ ያለበት ሌላው ሰው ሠራሽ ሐይቁን ሥነ ምኅዳርዊ ቀውስ የተዳረገው ወያኔ ትግሬና ተባባሪዎቹ ከመጡበት ከደርግ ውድቀት በኋላ በተለይም ባሕርዳር ከተማ የባንቱስታን አፓርታይድ ያማራ ክልል ተብዬው ዋና ከተማ ሆነች ተብሎ የሕዝብ ንብረት የነበረውን መሬት፣ ፋብሪካና ድርጅት ሁሉ ወያኔዎች ወደራሳቸው የግል ሃብትና ንብረት አዛውረው መበዝበዝ ሲጀምሩ ነው።

ቀጥሎም የወያኔ ትግሬ አናሳ ጎሣ መንግሥት ነኝ ባይ ብቸኛው የኬሚካል ማዳበሪያ ነጋዴ ድርጅት በጣና ሐይቅ ዙሪያና መገቢ ወንዞች አቅራቢያ ለሚኖሩ ገበሬዎች የማሳቸው ዐፈር እንኳ በባለሙያ ሳይመረመርና የሚያስፍልገው ማዕድናት ልክና መጠን ሳይታወቅ ሾላ በድፍን በግዳጅ ገዝተው በነሲብ በማሳቸው ላይ እንዲነሰንሱት በመደረጉ ምክንያት ናይትሬትና ፎስፌትን የያዘው ማዳበሪያ ዘወትር ዝናብ ሲጥል በጎርፍ ተጠራርጎ በቀጥታ የሚገባው ወደ ጣና ሐይቅ ሲሆን ይህም የምግብ ቁስ በሽበሽነት ያለው ሐይቅ (eutrophic lake) አስደርጎታል። በዚህም ረገድ ለውሃ አረሙ እምቦጭ እድገትና ቅጽበታዊ መስፋፋት ተስማሚውን ሁኔታ ፈጥሮለታል።

ከዚህም ሌላ በባሕርዳር ከተማ ውስጥ ያሉት የቤት ውስጥ፤ የብዙ ሆቴሎች፤ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችና የእንዱስትሪዎች ውዳቂ ፍሳሽ ሁሉ ያለምንም ማጣራት በቀጥታ ወደ ጣና ሐይቅ ይለቀቃል። እረ! ምን ይህ ብቻ በጣና ሐይቅ ዙሪያ ለአውሮፓውያን፣ ለአረቦች፣ ለይሁዲዎች፣ ለአሜሪካኖችና ለወያኔ ትግሬዎች ወዘተረፈ ከበርቴዎች ዘመናዊ የአበባ እርሻ፣ የቆዳ ፋብሪካዎችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች ሁሉም እንበለ ሕግ ውዳቂ ቆሻሻቸውን የሚጥሉት በጣና ሐይቅና አባይ ወንዝ ላይ ነው። ለምሳሌ በባሕርዳር ከተማ ውስጥ ካሉት ሦስት የቆዳ ፋብሪካዎች የሚለቁቀው ቆሻሻ ውሃ በአካባቢው ገበሬዎች ላይ ከፍተኛ የሕልውና አድጋ አድርሶባቸዋል። በክሮሚዬም ከባድ ብረታብረት መርዛም ነጥረ ነገር ዐፈሩና ውሃው በከፍተኛ ደረጃ ተበክሏል። የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቡና ዛፎች ደርቀዋል። የቀንድ ከብቶች በብዛት አልቀዋል። በጣም ብዙ የገበሬ ቤተሰቦች፣ ለዓይን፣ ለቆዳ፣ ለጨጓራ፣ ለልብ ወዘተረፈ በሽታዎች ተዳርገዋል።

የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ይባስ ብለው ጣና ሐይቅን በጠቅላላው ለማድረቅ ይኸው ያማራ ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶችና አገር በቀል ቅጥረኛ ተላላኪዎቻቸው ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት ማለትም በ2003 ዓ.ም ሆን ብለው ይህን መጥፎ ወራሪ አረም ገበሬው እምቦጭ (water hyacinth) ብሎ የሚጠረውን መገጭ ወንዝ አፍ ላይ አምጥተው ጣና ሐይቅን አስበከሉት። እስከአሁን ድረስ ከ50 ሺህ ሄክታር በላይ የጣና ሓይቅ ስፋት በአረሙ ተሸፍኗል።

ያካባቢው ገበሬዎች ብቻቸውን በአስገራሚ ሁኔታ በባዶ እጃቸውና እግራቸው፤ በጣም ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ከእባብ፣ ከጊንጥ፣ ከወባ ትንኝ፤ ወዘተረፈ ጋራ እየታገሉ አረሙን ባያርሙት ኖሮ መላው ሐይቅ ባላፋት ስድስት

ዓመታት ውስጥ ባረሙ ይሸፈን ነበር። ተመሳሳይ ድርጊት በጎረቤት አገሮች ላይ ተክስቷል። የአፍሪቃ አህጉር ትልቁ የቪክቶሪያ ሐይቅ ለአድጋ የተጋለጠውም የአውሮፓ ቤልጅግ ቅኝገዥ ሰፋሪዎች በሩዋንዳ ከአሜሪካ አህጉር አምጥተው በጓሮ ኩሬያቸው ላይ የተከሉት ወደ ቪክቶሪያ ሓይቅ ተዛምቷል። የዚህ መጥፎ የውሃ አረም የሥነ ዕፃዊ መጠሪያው (*Eichhiornia Crassipes*) ሲሆን በሕይቁ ላይ ፍተኛ ያካባቢ ብክለት በማስከተሉ ሳቢያ የኬኒያ ኪሲሙ ባሕርዳር ከተማ ያሣ ምርት አክትሞለት ነበር። ሆኖም ግን የኬኒያ፣ የዩጋንዳና የታንዛኒያ መንግሥታት አረሙን ለመቆጣጠር በጣም ከፍተኛ ወጭና ጥረት አድርገዋል።
የጣና ሐይቅ በእምቦጭ በመወረሩ ምክንያት ልክ እንደ ኬኒያው ኪስሙ የዓሣ ምርቱ ቀንሷል። በዓመት ከ 1454 ቶን በላይ የዓሣ ምርት ሲሰጥ የነበረው ጣና ሐይቅ ዛሬ ለገበያ የሚመጥን ዓሣ ማግኘት ባለመቻሉ ከወያኔ ትግሬዎች የግል ይዞታ ከተከዜ ወንዝ ግድብ የሚመረተው ዓሣ ለባሕርዳር ከተማ ገበያ በመቅረብ ላይ መሆኑን "ያማር ቴሌቪዥን" እና የጣና ሐይቅ በተሰኘ ርእስ www. zehabesha.com / amharic/?p=78285 ተዘግቧል። ይህም የወያኔ ትግሬን እቅድና ዝግጅትን በግልጽ ያመለክታል። በጣም የሚያስቆጣው ነገር ደግሞ የባሕርዳር ከተማ የወያኔ ታማኝ ግብር አበር ሃብታሞችና ባለሆቴሎች ሁሉ የተከዜ ግድብ ዓሣን አግበስብሰው እየበሉ ሠገራቸውን ጣና ሕይቅ ውስጥ መድፋታቸው ነው።

# እምቦጭ ምን ዓይነት አረም?

የውሃ አረሙ እምቦጭ ነፃ ተንሳፋፊና በቅጽበት ተስፋፊ፤ እጅግ በጣም በፍጥነት አዳጊና ተንሰራፊ፤ ከፍታው እስከሜትር የሚደርስ፣ ባለ ሰፊ፣ ወፍራምና ደማቅ አረንጓዴ ልስልስና አብረቅራቂ ቅጠልና በአብዛኛው ደብዛዛ ሓምራዊ አበባ ያለው በጣም አደገኛ ወራሪ ዕፅ ነው። ፍሬው ሳያበቅል እስከ 28 ዓመት ለመቆየት ይችላል። እምቦጭ ከፍተኛ ቅዝቃዜ ማለትም በበረዶ የተሸፈነና ጨውማ በሆነ ሕይቅና ኩሬ ለማደግ አይችልም። የንጹሕ ውሃ ሐይቅና የኩሬዎችን ገጽታ በአረሙ ከተሸፈኑ የፀሐይ ብርሃን ጠልቆ መግባትን፣ የውሃውን ዝውውርና እንቅስቃሴ ያግደዋል። ይህም ሂደት በሐይቁ ውሃ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን አኮስጅን መጠን ይቀንሰዋል። አየር የሚያስፍልጋቸውን እንስሳት ታፍነው ይሞታሉ። በዚህም መሠረት በተለይ አሣዎችና ረቂቅ ሕይዎ አካላት ዋና ተጠቂዎች ይሆናሉ። ከዚህም ሌላ በአረሙ የሚሸፈነው ውሃ ለወባ ትንኝ፣ ለዝሆኔ በሽታ አስተላላፊ ነፍሳት መራቢያ ስለሚሆን ለአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ የሚያስከትለው የጤና አድጋ ከፍ ያለ ነው። የጀልባ ጉዞም ይሰናከላል። የአረሙ ቅጠል ከፍተኛ መርዛም የሆኑ ኬሚካሎችን በመያዙ ምክንያት ለእንስሳት መኖ አይሆንም።

# ሐይቁን ለማዳን ምን ማድረግ ይገባል?

## የሚከተሉትን ርምጃዎች በተቀነባበረ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው።

### ሀ. እምቦጭ ለመቆጣጠር ምን ይደረግ?

አረሙን ለመቆጣጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ ሦስት ዘዴዎች ተሞክረዋል። **እነዚህም፤**
**አንደኛው** አካላዊ ( Physical) ማለትም ማረም ነው። ልክ የጣና ዙሪያ ገበሬዎቹ እንዳደረጉት እረሙን በውሃ ላይና የብስ የማረሚያ መኪና (Aquatic weed Harvesters ) እና ልዩ ልዩ አነስተኛ መሣሪያዎችና መለዋወጭያዎችን በመጠቀም አርሙን ነቅሎ ማስወገድ ነው።
ለምሳሌ የአሜሪካ ፋብሪካ በመላው ዓለም የሚሸጠው EcoHarvest የተባለውን ዋጋው 67 ሺህ ያሜሪካ ብር የሆነውን በአስቸኳይ ገዝቶ ሥራ ላይ ከማዋል የተሻለና ተስማሚ አማራጭ የለም።

**ሁለተኛው** ኬሚካላዊ ማለትም ፀረ አረም መጠቅም ነው። ይኸኛው ዘዴ ደግሞ ሌላ የጎንዮሽ አድጋ አለው። በሌሎች ዕፀዋትና እንስሳት እንዲሁም ሰዎች ላይ ሌላ ጉዳትን ስለሚያስከትል ተመራጭ አይሆንም።

**ሦስተኛው** ዘዴ ሥነ ሕያዊ (Biological) ማለትም የአረሙን ቅጠል የሚበሉ የባሕር ትንንሽ ፌንጣዎችንና ጢንዚዛዎችን አራብቶ በመልቀቅ ነው። ችግሩ ደግሞ እነዚሁ ሌሎች ጠቃሚዎቹን ነፍሳት የልዩ ልዩ ሰብል ብናኝ ተራክቦት / pollination/ አከናዋኞችን እንደ ንብ የመሳሰሉትን የማያጠቁ መሆናቸው በአስተማማኝ ሁኔታ ገና አልተረጋገጠም።

### ለ. ጠሰኛው የጣና በለስ ኃይል ማመንጭያ መዘጋት አለበት

ከጣና ሐይቅ የተፈጥሮ ግድብ ለጣና በለስ ኃይል ማመንጭያ 9.14 ቢሊዎን ኩባዊ ሜትር ውሃ ማለትም ሲሶው ተወስዶለት ይቅርና በበጋ ወራት የጣና ሐይቅ ጥልቀቱ እየቀነሰ የመርከብና ጀልባ መጓጓዣ ችግር በተደጋጋሚ መከሰቱ ይታወቃል። የጣና ሐይቅ በጣም አነስተኛ ጥልቀት ያለው መሆኑ በግልጽ እየታወቀ ሐይቁን ከሥሩ ሸንቁሮ ከፍተኛ የውሃ መጠን ለጣና በለስ ኃይል ማመንጭያነት ይወሰዳል። በዚህም ምክንያት ነው የሐይቁ ስፋቱ በፍጥነት እየቀነሰ የሄደው። ወያኔዎች ባሕር ሸሽ መሬቱን በሄክታር አየለኩ ለታማኞቻቸው አከፋፍለዋል።

የጣና ሐይቅ በሰው ሠራሽ አደጋ ለአጠቃላይ ሥነ ውሃዊና ምኅዳራዊ ቀውስ ተጋልጦ ልክ እንደ ቻድ ሐይቅ በመድረቅ ሂደት ላይ ይገኛል። በጥልቀቱ መቀነስና በውሃው ማነስ ሳቢያ የደሴቶች አየር ንብረት በጠቅላላው ይቀያየራል። ስለሆነም ለጣና በለስ የሚወሰደው ውሃ በአስቸኳይ ወይ መዘግጋት ያለበለዚያም ውሃ ተመልሶ ወደ ሐይቁ ካልገባ በስተቀር የጣና ሐይቅ ለአካባቢው ሕዝብ ሕልውና መሆኑ ያከትማል። ተፈጥሮ የሠራውን ግድብ ከሥሩ ነድሎ ውሃውን በገፍ ሙጥጥ አድርጎ መውሰድ ዋና የጠላት ሥራ እንጂ ከቶ ልማት እንዴት ሊሆን ይችላል? ሌላም ትልቅ ጉዳይ አለ። ከጣና በለስ የሚገኘው የኮረንቲ ጉልበት ለጎጃምና ጎንደር ከተሞች ጥቅም ሳይሆን ለሌሎች አካባቢዎችና በተለይም ለወያኔ ትግሬ የሱካር ፋብሪክ ኃይልና ሽንኮር አገዳ አቅርቦት መዋሉን መገንዘብ ያስፍልጋል። በጣና ሐይቅ ላይ የተፈጸመው ድርጊት ከዚህ ቀደም በአጤው ዘመነ መንግሥት የአባይ ወንዝ ሽለቆን ያጠኑት ያሜሪካ መሐንዲሶችን እቅድና ሃሳብ በፍጹም ተጻራሪ ነው።

## ሐ. ፍሳሽ ቆሻሻ ውሃ ወደ ሕይቁና ወንዙ የሚለቁት ሆቴሎች፣ ፋብሪካዎችና ድርጅቶች ይዘጉ

በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ ከስልሳ በላይ የሚሆኑት፣ በአብዛኛው ያማርኛ መጠሪያ ስምን ተጸይፈው የፈረንጅኛ ስያሜ ያላቸው ሆቴሎች ፍሳሽ ቆሻሻቸውን ያለምንም ማጣራት ወደ ጣና ሐይቅና አባይ ወንዝ ላይ እየለቀቁ የሚገኙት በአስቸኳይ መዘጋት አለባቸው። እስከ አሁን ላድረሱት ያካባቢ ብክላ ከፍተኛ የገንዘብ መቀጮያ መክፈልም ግዴታቸው ነው።
ከዚህም ሌላ የባሕርዳር ከተማ አስተዳደር የመኖሪያ ቤቶች፤ የድርጅቶችንና የእንዱስትሪዎችን ውዳቂ ፍሳሽ ማጣሪያ ሥርዓት /Waste-water treatment/ Swerage System / በአስቸኳይ መገንባት ይኖርበታል። የመንግሥት ልዩ ልዩ ተቋማት የሆኑት ለምሳሌ፤ ሃኪም ቤት፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ ወህኒ ቤቶች፣ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶ ወዘተረፈ. ፍሳሽ ቆሻሻቸውን ሳያጣሩ ነው ወደ ሐይቁና አባይ ወንዝ የሚለቁት።
የባሕርዳር ዩኒቨርስቲ ተብዬው ተቋም ጣና ሐይቅ በእምጭ አረም አንድ ሰባተኛው እጅ ከተበከለ አምስት ዓመት ዘግይቶ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ እንዲሉ አረሙን የሚበላ ጢንዚዛና ፌንጣ ለማራባት ሙከራ እያደረግሁ ላይ ነኝ ብሎ ከማሳወቁ ይልቅ በቅድሚያ በግቢው ውስጥ የሚፈጠረውን ፍሳሽ ቆሻሻ አጣርቶ ቢላቅ ምንኛ በተሻለ ነበር!

## መ. የኬሚካል ማዳበሪያ፤ የፀረ ተባይና የጸረ አረም መዘዞች

በጠና ሐይቅ ዙሪያና ገባሪ ወንዞዞቹ አቅራቢያ የሚኖሩ ገበሬዎች ከተፈጥሮ ፍግና ብስባሽ (Organic manure) ዐፈር ማዳበሪያ በስተቀር ምንም ዓይነት ኬሚካላዊ ማዳበሪያ፤ ጸረ አረምና ፀረ ተባይ ኬሚካል እንዳይጠቀሙ በሕግ የተከለከለ መሆኑን በሰፊው ማሳወቅ፤ ማስተማርና መቆጣጠር ግዴታ ነው። ጣና ሐይቅ ላካባቢው ሕዝብ የመጠጥ ውሃ ምንጭ በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ መጠበቅ ይኖርበታልና። ገበሬዎች በጣና ሐይቅ ዙሪያ የወደሙ ደኖች በስፋት ዳግም እንዲደንኑ፤ ያፈር እጥበትን ለመከላል ሣር እንዲዘሩ ከፍተኛና ዘላቂ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

## ሠ. የግብርና መሬትና የከተማ ቦታ ይዞታ ባለቤትነት ባማራ አገር

ያለፈው የደርግ ኮሚኒስት ነኝ ባይ መንግሥት በጅምላ የገጠር መሬትን፣ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን፣ የልማትና፣ የማምረቻና ማከፋፈያ፣ የንግድና የአገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን ያለአግባብ ወርሷል። የወያኔ ትግሬ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ተብዬው ሥልጣን ሲይዝ በራሱ ክልል ውስጥ የተወረሱ ንብረቶችን ለባለቤቶቹ ሲመልስ በሌሎች ክልሎች ግን ተመላሽ አላደረገም። የሽግግር መንግሥት ነኝ ካለበት ጅምሮ አስከዛሬ መሬት ሁሉ የመንግሥት ነው ብሎ ለም የርሻ መሬት ከገበሬው በገፍ እየተዘረፈ፣ ከተሜውም ከመኖሪያው አየተፈናቀለ በኪራይና በሊዝ ወያኔ ትግሬዎች ለውጭ ከበርቴዎች ቸብችበውታል። በነገራችን ላይ የወያኔ ትግሬ ባንዳ ውላጅ ቀንደኛ መሪ መለሰ ዜናዊ ከቀጣሪው ያሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን አቶ ኸር ማን ኾኽን ጋራ ባደረገው ውይይት ላይ በኢኮኖሚው መስክ የነፃ ገበያ ሥርዓት መሠረት ስለምን መሬት የግል ሃብትና ይዞታ አታደርግም ብሎ ላቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምልሻ "ዐማሮች ዳግመኛ መጥተው እንዳይወስዱት ነወ" ማለቱ አይዘነጋም።
የወያኔ ትግሬዎች ዋና ዓለማና ፍላጎት ኢትዮጵያውያንን በተለይም ዐማራውን ማኅበረሰብ ባገሩ ምድር ባይተዋር በማድረግ ያለጠርነት ለውጭ ሀገርና አቀባባይ ትግሬ ከበርቴዎች ለም መሬቱን አስረክቦ እራሱን ለባርነትና ድህነት ዳርጎ እንዲኖርና ቀስ በቀስ እንዲጠፋላቸው አቅደዋል።
ስለዚህ ዐማራው ማኅበረሰብ የተዘጋጀለትን ሴራ ተገንዝቦ እንደ ባሕሉ ርስት በሺህ ዓመቱ ለባለቤቱ ነውና በማራው ክፍለ ሀገራት የገጠር መሬት በግል ይዞታ ለገበሬው መሰጠት እንዳለበት ተባብሮ መነሳት አለበት። የመንግሥት ተብዬ ቅጥረኛ ጉጀሌ ጭሰኛ መሆን ይብቃ።
ዐማራው ኢትዮጵያዊ ሕዝብ በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቶት ያለማውን የእርሻ መሬትና የከተማ ቦታ በግል የመያዝ፣ ይህንንም ይዞታውን ያለአንዳች ገደብ መሸጥና መለወጥ፣ የማውረስ መብቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ገበሬው የመሬቱና የግል ሃብት የይዞታ መብቱ ሲረጋገጥለት ለአካባቢው ሥነ ምኅዳር ጥበቃና እንክብካቤ አስተማማኝና ቀጣይ አስተዋፅኦ ያበረክታል።
ያማራው ማኅበረሰብ ከወያኔ ትግሬና ግብረበላዎች ጭሰኝነት፣ ጥገኛነት፣ ተስፋፌነት፣ የዘወትር ተፈናቃይነትና ዓይን ያወጣ ብዝበዛ ነፃ መውጣት ለጣና ሐይቅና አባይ ሸለቆ ያካባቢ ደህንነት ወሳኝ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል።

ግራዋ ሣሙኤል
ድክተር ኢንጅኒየር